# አገር እንዴት ሰነበተች ቁጥር 46

ታህሳስ 23 ቀን 2015ዓም (01-01 2023)

ከሁሉ በፊት የኢትዮጵያ አንድነት ራዲዮ ስርጭት ለሁሉም ኢትዮጵያዊ እንኳን ለፈረንጆቹ 2023 ዓም አደረሳችሁ፣ዓመቱም የሰላምና የጤና ያገራችንንም ትንሳኤ የምናይበት ይሁንልን በማለት መልካም ምኞቱን ይገልጻል።

አዎ መልካም መመኘት ተፈጥሮያዊ ነው።ግን ምኞት ብቻውን ለሚፈልጉት ውጤት አያበቃም። ከምኞትና ፍላጎት ጋር አብሮ የሚሄድ ጥረትና ትግል ማድረግ ግድና አስፈላጊ ነው። መብላት የሚፈልግ ሰውም ሆነ እንስሳ የሚመኘውን ምግብ ሊያገኝ የሚችልበትን መንገድ ካልፈለገና ጥረት ካላደረገ በርሃብ ይሞታል እንጂ በመመኘቱ ብቻ የሚፈልገውን ምግብ አግኝቶ ጠግቦ ሊያድር አይችልም።ጥረት ካደረገና የሚፈለግበትን ካሟላ ምኞቱን ወደ ተጨባጭ ውጤት ለመለወጥ አያዳግተውም።እንኳንስ የሰው ልጅ ቀርቶ አውሬም እራቡን የሚገታው ከዋሻው ወጥቶ ለአደን ሲሰማራ ነው። በዋሻው ውስጥ ተቀምጦ ቢመኝ የሚበላውን አያገኝም።በሁሉም ዘንድ ምግብን እንደምሳሌ አቀረብን እንጂ የሰው ልጅ ፍላጎቱ በሆዱ ብቻ ተወስኖ ይቀራል ማለታችን አይደለም። ለመኖር የሚያስፈልጉት አያሌ ቁሳዊና መንፈሳዊ ግብአቶች ያስፈልጉታል።እነዚያንም ለማግኘት ሲል ጥረት በማድረጉ የብዙ የፈጠራ ችሎታዎችና ምርቶች ባለቤት ለመሆን በቅቷል። ለዚያም ነው የሰው ልጅ ከእንስሳት የተለዬና አስተዋይ ፍጡር ነው የሚባለው።ለመብላት ማምረት እንደሚያስፈልግ ሁሉ ለማምረት ደግሞ የሚያመርቱበት መሬት፣መሣሪያና ውሃ መኖር ወሳኝ ነው።መሬት ብቻ መኖሩ ሳይሆን በመሬቱ ላይ የመጠቀም መብት ካልተረጋገጠና ሰላማዊ ኑሮ መኖር ካልተቻለ አርሶ መብላት፣ ነግዶና ሠርቶ ማደር፣ለተሻለ ኑሮ መብቃት አይቻልም።ጤነኛ ኑሮ ለመኖር በሽታን ለመከላከል መድሃኒት መፍጠርና መጠቀም እንዲሁም ንጽህና መጠበቅ ተገቢ ነው።ከድንቁርና ለመውጣት እውቀት መቅሰምና መማር ዋናው መፍትሄ ነው።ይህ ሁሉ የሚቻለው በባለቤትነት ታውቀው የሚኖሩበት አገር ሲኖር ነው።ለዚያም ነው ከጥቂት ዓመታት ወዲህ አገር የሆኑት ደቃቃ አገሮች ሳይቀሩ በሁሉም ዘርፍ አድገውና ተለውጠው ሕዝባቸውም በተሻለ ደረጃ ላይ ለመኖር የበቁት።

ኢትዮጵያውያን ለገጠመን ዘርፈ ብዙ ችግርና ላለንበት ምስቅልቅል ሁኔታ የዳረገን የአገር ባለቤትነታችን በጥቂት አምባገነኖች በመገፈፉ ነው።አገር የሚባለው የሁሉም የጋራ ንብረት በጥቂት እራስ ወዳዶችና አገር ጠሎች ፍላጎት መዳፍ ሥር ወድቆ ብዙሃኑ ያሰብነውና የምንመኘው መልካም ቁሳዊ ነገር ቀርቶ ሰብአዊና የዜግነት መብታችን ተደፍሮ አገር አልባ የምንሆንበት የጥፋት ጎዳና በመዘርጋቱ ነው።

ጠላቶቻችንና አምባ ገነኖች በሚጭኑብን የሴራ ተልእኮ ቅስማችን ተሰብሮና አንድነታችን ተናግቶ አምርተን መብላት ስንችል ለልመና እጃችንን እንዘረጋለን።ከዚያም አልፎ ተርፎ የሰውነት ማንነታችንን ጥለን በጎሳ ማንነትና በሃይማኖት ምክንያት እርስ በርስ እንጨፋጨፋለን።ላለፉት 50 ዓመታት ተሸክመን የዘለቅነው ይህ ፈተና አሁን ከመጨረሻው ጥግ ላይ አድርሶናል።

ባለፉት ዓመታት በተለይም ባለፉት አራት ዓመታት ያለውን ሁኔታና ሊከሰት የሚችለውን አደጋ በሚቻለን መጠን እዬተነተን መፍትሔ የሚሆኑትንም ሃሳቦች እያቀረብን ቆይተናል።እራሳችንን ከመለኮታዊ ችሮታ ጋር የተያያዘ ትንቢት ተናጋሪ ነብይ በማድረግ ሳይሆን ፣በፖለቲካው ዙሪያ ግን ሊሆን የሚችለውን ስንተነብይ ቆይተናል።ሌሎቹም እንደኛ ሊሆን የሚችለውን ክስተት በቅድሚያ ሲተነብዩ ኖረዋል።ለዚያ ትንቢያ በሃቅ ላይ የተመሰረተ ማስረጃ፣ክትትል፣ድፍረትና እውቀት ወሳኞች

ናቸው።ችሎታ ኖሮ ሃቀኝነት ከሌለ፣ለግል ጥቅምና ደስታ ብቻ ከዋለ ትንቢቱን የተንሸዋረረ ያደርገዋል፤ ሕዝብንም ያሳስታል፤የአምባ ገነኖች መጠቀሚያ ያደርጋል።ይህ በብዙ ምሁራን ላይ የሚታይ ድክመት ነው።

አብይ አህመድ አሊ የሚመራውን የኦነግ ኦሕዴድ ኂላም ላይ ብልጽግና ስብስብ ገና ከጅምሩ የሚመራበትን ሕገጥፋት፣ የጀርባ አሰላለፍና ታሪክ መርምረን ለአገራችንና ለሕዝባችን መልካም ለውጥ ሊያመጣ እንደማይችል ተናግረናል።እንደውም ከወያኔዎቹ በባሰ ደረጃ እያጭበረበረ ገደል የሚከት መሆኑን ደጋግመን አሳውቀናል።በተለይም ከሁለት ዓመት ወዲህ ሁለቱ ጸረ ኢትዮጵያ ቡድኖች የከፈቱት የእርስ በርስ ጦርነት የጥቅምና የሥልጣን ሽኩቻ መሆኑንና በመጨረሻም ላይ ተደራድረው ለሃያ ሰባት ዓመት የዘለቁበትን የኢሕአዴግ ሥርዓት በብልጽግና ካባ እንደሚያስቀጥሉ መናገራችን የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ሲሆን ዝርዝሩ በስርጭታችን ሳጥን(አርኪፍ) ውስጥ ይገኛል። ብልጽግና የኢሕአዴግ ቁጥር አንድ ተከታይ ቁጥር ሁለት መሆኑንም ገልጸናል።ከሁለት ሳምንት በፊትም ሆነ በኂላ በኬንያ ያደረጉትን ስብሰባ ወዴት ሊያመራ እንደሚችል አንስተን በአሜሪካኖችና በምዕራብ አውሮፓውያኖች ፍላጎትና ትዕዛዝ ስር የወደቀ ስምምነት እንደሚያደርጉ በዋናነት የአማራውን አጽመ-ርስቶች የሆኑትን የወልቃይት፣ጠገሌና የራያና ቆቦ መሬቶችን ነጥቆ ለወያኔ ለመስጠት እንደሚስማሙ ተናግረን ነበር።ያልነው አልቀረም ያንን ለማድረግ ዝግጅቱ ከዳር ላይ ደርሷል። ፋኖና የአማራው ልዩ ሃይል ከቦታዎቹ እንዲለቁ በሃይል ጭምር እርምጃ ለመውሰድ እንደታቀደ አስጠንቅቀን ነበር።ያም በተግባር እዬታዬ መጥቷል። ለአማራው መብት ይቆማሉ የተባሉትን ሁሉ በገጠርም በከተማም የሚገደሉትን ገሎ የሚያፍነውን አፍኖ ሌሎቹንም በማሳደድ ቦታውን አጽድቶ ለማስረከብ ሥራው ተጀምሯል።የቀረው በሕገ መንግሥቱ መሠረት የሚል ሽፋን ሰጥቶ ማጽደቅ ነው።

ስምምነቱን ተከትሎ ወያኔን አሸባሪ ብሎ የሰዬመው ፓርላማ አፈጉባኤ፣ፓርላማ ከማለት የአሳማዎች ጉረኖ ወይም በረት ማለቱ ተገቢ ይመስለናል ሌሎቹን የኦነግ ኦህዴድ ብልጽግና ባለሥልጣኖች አስከትሎ መቀሌ መግባቱ ሲገርመን አቀራረባቸው እንኳንስ ከሚሊዮን በላይ ህይወት የጠፋበት ጦርነት ያካሄዱ የጦር ወንጀለኞች፣እርስ በርሳቸው የስድብ ናዳ ሲወራወሩ የከረሙ ጠላቶች ቀርተው የናፈቀ ዘመድም ቢሆን እንደዚያ በጋለ ፍቅርና ናፍቆት ይተቃቀፋሉ ብሎ የገመተ አልነበረም። ለፈጸሙት ወንጀል ይቅርታ መጠዬቅ ቀርቶ በነሱ ምክንያት ለጠፋው ሕይወት በማዘንና በመጸጸት ያሉት የለም።ከሚሊዮን በላይ የረገፈው የዜጎች ህይወት ለሁለቱ አገር አጥፊ ሃይሎች የፖለቲካ ጋብቻ የተጣለ ጥሎሽ ሲሆን፣ወልቃይትና ጠገሌ፣ራያና ቆቦም የጫጉላ ቤት ሽልማት ተደርገዋል። በዚህ ውጤት ወያኔ ብር አምባር ሰበረልዎት እያለ ሲጨፍር የኦነግ ብልጽግናው የከሰረ ሰልፈኛ ደግሞ አሶስጄ መጣሁ አሶስጄ፣ አምባሬን ከጄ እያለ ባዶ እጁን እያጨበጨበ ቦሌ ገብቷል።የስምምነቱ ልክ በዚህ ብቻ የሚገታ ሳይሆን የወያኔ መሪዎች በመካከለኛው መንግሥት ተብዬው የሥልጣን እርከን ውስጥ የሚገቡበትንም ዕድል ያረጋገጠ ነው።ወያኔ የኤኮኖሚ ጥቅሙን ካላስመለሰ፣እንዲሁም በሚፈልጋቸው ቁልፍ ያገሪቱ አመራር ቦታዎች ላይ ካልተቀመጠ ለስምምነት ፊርማውን እንደማያስቀምጥ የተናገርነውን በገሃድ አይተናል።ይህንንም ተከትሎ አብይ አህመድ የሚመራው መንግሥት የሚኒስትሮች ሹም ሽር ለማድረግ ተገዷል።ማንን አሰናብቶ ማንን እንደሚያስቀምጥ ምደባው ተጠናቋል።በእኛ በኩል ወያኔ ጥርስ የነከሰባቸው፣ ለሥርዓቱ መጠላት ምክንያት የሆኑና ሕዝብ አንቅሮ የተፋቸው፣ ያገልግሎት ዘመናቸውን የጨረሱት ዋጋ ቢሶች ሊሆኑ ይችላሉ የሚል ግምት አለን። እንደ ደመቀ መኮንንና አገኘሁ ተሻገርን የመሳሰሉትን አጋሰሶች የተሸከሙትን የሥልጣን ሸቀጥ አራግፎ እንደሚያባርራቸው ቀደም ሲልም ደመቀ መኮንን ሊባረር ከውጭ ጉዳይ ቢሮ በር ላይ እንደቆመ ተናግረን ነበር፤የሚወጡትም ፍንጮች ያንኑ ያመላክታሉ። የአብይ አህመድ "ተጠቅመህበት ወርውረው!" የሚለው ፍልስፍና በዚህ ይገለጣል።

የወያኔዎቹም ሆነ የአውሮፓና የአሜሪካኖቹ አንዱ ፍላጎትና ጥያቄ የአማራ ፋኖና ልዩ ሃይል እንዲሁም የኤርትራ  ጦር ከትግራይ መሬት ለቆ ይውጣ  የሚለው ነው።ለዚህም ጥያቄ አብይ አህመድ ሲፈልጉ በውድ አለዚያም በግድ አስጣለሁ የሚል ቃል ገብቷል።በቅድሚያ አማራውን ለማስጣት እርምጃ የወሰደ ሲሆን  በኢሳያስ ላይም ተግባራዊ ለማድረግ ከወያኔ ጦር ጋር የራሱን ጦር አስተባብሮ ለመዝመት የሚያመላክቱ መረጃዎች በመታዬት ላይ ናቸው።አብይ አህመድ ለሥልጣኑ ሲል እንኳንስ ኢሳያስን የናቱን ልጅ ወይም የራሱን ልጆች አሳልፎ እንደሚሰጥ በተደጋጋሚ ገልጸን ስለነበር ለእኛ አዲስና እንግዳ አይሆንብንም።እንግዳ የሚሆንብን እውነት ወያኔዎች ከአብይ ጋር ሆነው ኢሳያስን ይወጋሉ? ከወደፊቱ ዓላማቸው አንጻር የትኛውን ይመርጣሉ?የትኛውስ ይቀርባቸዋል?የሚለው ጥያቄ ሲሆን ውጤቱን የምናዬው ይሆናል።ለጊዜው ኢሳያስን ለማሶገድ ሲባል፣ከጥቅማቸው አንጻር የአውሮፓውያንን በተለይም የአሜሪካኖችን ፍላጎት ለማሟላት  ሲሉ ለመዋጋት ቢነሱ ሊጠቀሙበት የሚችለው አንዱ መንገድ የኢሳያስ ተቃዋሚ ከሆኑትን ኤርትራውያን ጋር ግንባር መፍጠር  ይሆናል። ያም ሲነሱ ላቀዱት ትግራይ ትግሪኛ ሃገር ምሥረታ መንደርደሪያ ይሆናቸዋል።ሌላው የኤርትራ ሕዝብ ይቀበል አይቀበል በጊዜው የሚታይ ይሆናል።እርግጠኛ ሆኖ መናገር የሚቻለው ወያኔ በቦታው ወሳኝ የመሆን ዕድል ካገኘ ከታመቀው ሕዝባዊ ብሶትና የጎሳ መንገጫገጭ ጋር ተደምሮ ኤርትራ ከባሰ ቀውስና ችግር ውስጥ ልትገባ እንደምትችል ነው።

ለኢትዮጵያም ሆነ ለኤርትራ ህልውና የሚበጀው ነገር ወያኔንና ኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግናን አሶግደው በተሻለ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ስር በፌዴራል ደረጃ  ቢጣመሩ ነው።ይህ የትልቅ አገር፣የብዙ የተፈጥሮ ሃብትና ማዕድን፣የለም መሬት ፣የባህር ወደብ፣ ችሎታ ያለው የብዙ ሕዝብ ባለቤት ያደርጋቸዋል።በከባቢው ቀርቶ በዓለም መድረክ ተደማጭነታቸው የጎላ ይሆናል።ይህንን ሃሳባችንን ኤርትራውያንና ኢትዮጵያውን ከልብ ሊያጤኑት ይገባል እንላለን።ምዕራባውያንም ሆኑ ሌሎቹ አገራት ኢትዮጵያና ኤርትራ እንዲዳከሙ፣እንዲበታተኑ እንጂ  አብረው እንዲጠነክሩና በራሳቸው እንዲቆሙ አይፈልጉም።ያንን መስበር የሚቻለው በፌዴራላዊ ግንኙነት ብቻ ነው።የአጭሯ ጊዜ መቀራረብ እንደምልክት ሊወሰድ ይቻላል።ከዚያም በተረፈ በታሪክ፣በሃይማኖት፣በመዋለድ ተሳስሮ አብሮ መኖሩን፣የስም ፣የባህል፣ያመጋገብና ያለባበስ እሴቶች ከምንለያይበት ጥቂት ምክንያት በላይ ጎልተው የሚታዩ የምንቀራረብባቸው የጋራ እሴቶቻችን ናቸው። የሰላሳ ዓመት የድንበር አጥር የዘመናት አብሮነታችንን ሊገታው አይገባም።

ከሁሉም በላይ ልብ የሚሰብረው ነገር የትግራይም ሆነ የኢትዮጵያ ሕዝብ  እነዚህ ሁለት አውሬዎች በአገርና በሕዝብ ስም በቀሰቀሱት ጦርነት በሚሊዮን የሚቆጠር  ዜጋ ሕይወት መጥፋቱን፣አካለጎደሎ መሆኑን፣መፈናቀሉንና ንብረት መውደሙን   ዘንግቶ ያንን የፈጸሙትን ወንጀለኞች በሕግ መጠዬቅ ሲገባው የሰላም አባቶች አድርጎ መቀበሉ ነው። ይህ በራሱ የሕዝቡን ስነልቦናና የማመዛዘን ችሎታ በቅጡ እንድንመረምረው ያስገድደናል።ከአንድም ሁለት ሦስት ጊዜ በተደጋጋሚ የሚጭበረበር ሕዝብ ስናይ ጉድለቱ ከአጭበርባሪው ሳይሆን ከራሱ ከተጭበርባሪው ነው ከሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ተገደናል። እዚህ ላይ አንድን አገር ወይም ሕዝብ እወክላለሁ የሚል መንግሥት ወይም ድርጅት ምን ማድረግ እንደሚገባው የሚያሳይ የሰሞኑን በቀድሞዋ ዩጎዝላቪያ አብረው ኖረው ከሰላሳ ዓመት ወዲህ እንደ ኢትዮጵያ የጎሳ ፖለቲካ ለያይቷቸው አገራቸው ፈራርሳ በጠላትነት ጎራ በተሰለፉት በሰርቦችና አልባንያ ጎሳዎች መካከል የተፈጠረውን ለማንሳት እንወዳለን።ኮሶቮ በምትባለው ብዙ አልባንያኖችና ሌሎቹ የጥንቷ ዩጎዝላቪያ ዜጎች በአንድነት በሚኖሩባት ከተማ የበላይነቱን የያዘው የአልባንያኑ ጎሳ ኋላ በከተማ በሚኖሩ  ቁጥራቸው አናሳ በሆነው ሰርቦች ላይ ጭቆናና በደል ሲደርስባቸው በትልቋ የሰርብ ግዛት የሚኖረው የሰርብ መንግሥት ከመቃወም አልፎ አልባንያውያኑን በጦር በማንበርከክና በመቅጣት የዜጎቹን መብት ለማስከበር ሲል የመከላከያ ሃይሉን ማሰለፉን ታዝበናል። በዚሁ ባልካን በተባለው

ከባቢ ያለፉት ሁለቱ የዓለም ጦርነቶች የተነሱበት ቦታ በመሆኑ ለሦስተኛውም የዓለም ጦርነት መነሻ ይሆናል የሚል ስጋት በመኖሩ በአውሮፓ ህብረትና በዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ጥረት ለጊዜው ጦርነት ሊቆም ችሏል፤ይህ ማለት ግን እስከመጨረሻው ጦርነት አይኖርም ማለት አይደለም። የጎሳ ክፍፍል እስካለ ድረስ በዬጊዜው ንትርክና ግጭት ላለመኖሩ ዋስትና የለም።

እዚህ ላይ ለማሳዬት የወደድነው አንድ ድርጅት ወይም መንግሥት ቆሜለታለሁ ለሚለው ሕዝብ እስከምን ድረስ ሊሄድ እንደሚችል ለማሳዬት እንጂ የጎሳ ንትርኩንና ክፍፍሉን ደግፈን አይደለም። በተጨማሪም በአገራችን ባለው ተመሳሳይ የጎሳ ፖለቲካ ምክንያት በአማራው ላይ በሚደርሰው ጭፍጨፋና በደል ላይ ለአማራው ቆሜያለሁ የሚለው ብአዴን በተባለ ከንቱ ስብስብ በስሙ ሥልጣን ለያዘበት ወገን ፣ለአማራው መብትና ደህንነት ከመቆም ይልቅ ለጨፍጫፊዎቹ ጥብቅና በመቆም የሰጠውን የክህደት መልስ ለማሳዬት ነው።እንደዚሁ ከንቱ የቭአዴን ስብስብ የአብይ አህመድ ፍላጎት በሥልጣኑ ላይ መቆዬትና የኦነግ ኦህዴድን የነጻ አገር ምሥረታ ማስቀጠልና ተግባራዊ ማድረግ ነው። ለዚያ ሲል አሳልፎ የማይሰጠው የኢትዮጵያ ተቋምና አገራዊ ህልውና የለም።ይህንን ዓላማውን ለመተግበር ለሚያስፈልገው ወጭ በኢትዮጵያ ስም ምዕራባውያን አገሮችና የገንዘብ ተቋማት ለሚሰጡት ብድርና እርዳታ ቀብድ የሚያሲዘው የኢትዮጵያን ልዑላዊነት ነው።

በተጨማሪም ድርጅቶችን በመሸጥ ኢትዮጵያ የነበራትን ሙሉ ባለቤትነት አሳጥቷል፤ የቀሩትንም ለመሸጥ በዝግጅት ላይ ነው። የመሸጥ አደጋ ከሚያንዣብብባቸው ተቋማት መካከል አንዱ የኢትዮጵያ አዬር መንገድ ነው።ወዳጅህ ሲታማ ለእኔ ብለህ ስማ እንደሚባለው የኬንያ አዬር መንገድ ለአሜሪካኑ ኩባንያ ለዴልታ አዬር መንገድ ለመሸጥ የንብረት ቆጠራውን ዜና ስንሰማ፣ ነገ በኢትዮጵያ አዬር መንገድ ላይ ሊደርስ የሚችለውን ተመሳሳይ እርምጃ አመላክቶናል።እንደነገሩማ የኬንያ አዬር መንገድ 33% ባለቤት የሆነው የኔዘርላንዱ አዬር መንገድ ኬ ኤል ኤም (klm) ነው።በዚህ የሩብ ተመን የተጀመረው ሽያጭ አሁን ለአጠቃላዩ ሽያጭ ማለማመጃ ሆኗል።መሪዎቹ ኬንያ አዬር መንገድ የአፍሪካ ኩራት (Kenian Airways an Afrikane Pride )የሚል ሎጎ የተሸከመውን የአገር ንብረት ሸጠው የበሉ፣የባርነት ሰንሰለትን እንደ ባህላዊ ጌጥ የተቀበሉና የሚኮሩበት ለመሆናቸው ብዙ ማስረጃዎችን መጥቀስ ይቻላል።የኬንያ መሪዎች እንደ ኢትዮጵያ መሪዎች በሙስናና ሌብነት የተጨማለቁ ስለሆነ አያስገርምም። የኬ ኤል ኤም KLM አየር መንገድ የእሩብ ድርሻ ቢኖረውም ፣የዓለም ኩባንያዎች የተሳሰሩበት የጥቅም ገመድ እረጅምና ብዙ ስለሆነ ከአሜሪካኖቹም የዴልታ አዬር መንገድ ጋር በትብብር ስለሚሠሩ ካለደቾቹ ፈቃድና እውቅና ብሎም ተሳታፊነት የተከናወነ ነው አንልም።ከከፈሉት የበለጠ የሚያገኙበት ከሆነ ደንታ የላቸውም።የኬንያ ባለሥልጣኖች ላልተጨነቁባት ኬንያ ደቾቹ ይጨነቃሉ ተብሎ አይታሰብም። በተመሳሳይም አብይ አህመድን የመሰለ ከሃዲ፣ ዘራፊና አዘራፊ ሥልጣኑን በተቆጣጠረበት አገር ለብቻው የሚንቀሳቀሰው የኢትዮጵያ አዬር መንገድ ከዚህ የተለዬ እጣ ፈንታ ይኖረዋል ብለን አንጠብቅም።ባለፈውም ስርጭታችን ስለ አዬር መንገዱ ትርፋማናት የተሰራጨው ወሬ ለሽያጩ የማስታወቂያ መንደርደሪያ ነው ማለታችን አይረሳም።የሠራተኞቹም አድማ ከዚህ ስጋት ጋር ሳይተሳሰር የቀረ አይመስለንም፤ሁሉንም በቅርቡ የምናዬው ይሆናል።

ለሱዳኖች የወረሩትን ለም መሬት እውቅና የሰጠ፣የአባይ ግድብን በግብጾች ፍላጎትና ቁጥጥር ላይ የጣለ ከሃዲ ሰው ለብሔራዊ ክብር ይቆማል ማለት ዘበት ነው።የሱም ብቻ ሳይሆን በፖለቲካ ድርጅትነት ስም አገሪቱን ያጥለቀለቁት ሳይቀሩ የፖለቲካ ድርጅት ሚናቸውን ከመወጣት ይልቅ የአብይን በጎ ፈቃድና ችሮታ ማሳደዱን መርጠዋል።እነዚህ የፖለቲካ ድርጅቶች ሳይሆኑ የንግድ ድርጅቶች ናቸው ለማለት ተግባራቸውን ያዬ ይደፍራል። ባለፈው ስርጭታችን እንደምሳሌ የጠቀስነው የኢትዮጵያ ሶሻል ዴሞክራቲክ ፓርቲ መሪ የሆነው በዬነ ጴጥሮስ የተባለ ጉፋያ፣የሶሽያል ዴሞክራሲን

ጽንሰ ሃሳብ ገደል ሲከት ታዝበን ጉድ ጉድ ስንል፣ በዚህ ሳምንት ውስጥ ደግሞ በአንድ የውይይት ዝግጅት ላይ ቀርቦ ስለፌዴራሊዝም ሲገልጽ "ይህ ያገራችን የጎሳ ፌዴራሊዝም ትክክልና ተገቢ ነው" በማለት የሚቃወሙትን ሁሉ አውግዟል። በዛም አልቆመም የአሜሪካንን የክፍላተ ሃገራዊ (States Federation)) የአስተዳደር ፌዴራሊዝምን ከአገራችን የጎሳ ፍድራል መንግሥታዊ አወቃቀር ጋር በማመሳሰል እንደምሳሌ አቅርቧል።እንዲያ ነው ከገሙ አይቀር ብስብስ!አሜሪካ እኮ የጎሳ ፌዴራሊዝም የላትም እንዳንለው ከኛ ያነሰ እውቀት ኖሮት ሳይሆን አድርባይነት ስላወረው ሲተራመስ ከባሰ አሮንቃ ውስጥ ይገባል በማለት አዝነን አልፈነዋል።እውነቱን አጥቶት ሳይሆን ያገኛት ቁራሽ ሥልጣን አስጨንቃው እንደሆነ እናምናለን።እንዲያ ነው የይሁዳ ልጅ! ይንን ከሃዲ አድርባይ እወክለዋለሁ የሚለው ሕዝብ መጠዬቅ እንዳለበት ለማሳሰብ እንወዳለን።

ሌሎቹም የፖለቲካ ፓርቲ ነን ባዮች ትንሽ የፖለቲካ ድርጅትነት ህዋስ በውስጣቸው የለም እንጂ ካለ ሲሆን ሲሆን የሕዝቡን ትግል መምራት አለያም ማጀብ በተገባቸው ነበር።የአሥር ዓመት ህጻን ተማሪ ሞትን ሳይፈራ አደባባይ ወጥቶ አንድ አገር! ፣አንድ ሕዝብ! ፣አንድ ሰንደቅ ዓላማ! እያለ ከአውሬ የሥርዓቱ ገዳዮች ጋር ሲጋፈጥ እነሱ እንደ ኤሊ ድንጋይ ለብሰው መቀመጣቸው ለትዝብት ጥሏቸዋል። የ1997 ቱን የቅንጅት ታሪክ ቢያስታውሱት መልካም ነው።አለበለዚያ ተቃዋሚ ነን የሚለውን ታፔላ በአጋርነት ታፔላ ቢለውጡት የተሻለ ይሆናል።ዱሮስ ቢሆን የህወሃትና የአነግን ሕገ-ጥፋት ተቀብሎ ፈቃድ ካገኘ የፖለቲካ ድርጅት ስብስብ ምን ይጠበቃል? ሌላው ማጭበርበሪያቸው የሰላም ትግል የሚለው ትርጉመቢስ አባባላቸው ነው።ያንንም ቢሆን በአደባባይ ሕዝባዊ ተቃውሞ በመጥራትና በመምራት አላሳዩም።ኢትዮጵያ ለመበታተን ስትንደረደር(ስታሽኮበኩብ)የፖለቲካ ጥያቄ መልስ ሲያጣና ሕዝብ በስርዓቱ ሲገደል፣ሲፈናቀል፣በማንነቱ ግፍና መከራ ሲደርስበት በሰላማዊ ትግልና ውይይት ለውጥ አመጣለሁ ማለት ጅልነት ወይም አድርባይነት ነው።የመንግሥት ፖለቲካ በአመጽ ታጅቦ ሕዝብ ሲያጠቃ፣ ተቃዋሚ ነኝ፣ለስርነቀል ለውጥ ቆሜያለሁ የሚል ሃቀኛ ፓርቲ ቢኖር የራሱን ሕዝባዊ አመጽ ለመምራትና ለማካሄድ በደፈረ ነበር። አመጽ የፖለቲካው ትግል ቅጥያ ጉልበት መሆኑን የትግል ሀሁ የቆጠረ አይከደውም።ሌላው ቢቀር ምንም ለመጥፎ ዓላማ ቢሆንም ከወያኔዎቹና ከአነጎቹ ብልጽግና መማር ይቻላል።

የፖለቲካ ድርጅት ማለት የራሱ መርህ ያለው፣ ለሕዝብና ለአገር ጥቅም የቆመ፣ በሥልጣን ላይ የተቀመጠን ጎጂ ቡድንና ሥርዓት ለማሶገድ የሚታገል ፣በራሱ እምነትና ዓላማ የሚንቀሳቀስ እንጂ በሥልጣን ላይ የተቀመጠ አምባ ገነን ቡድን ፈቃድ ሰጥቶት ወይም ነስቶት የሚወጣና የሚገባ ስብስብ ማለት አይደለም።ከሃምሳ በላይ የሆኑ በፖለቲካ ድርጅትነት ስም የተሰለፉ ድርጅቶች ከሰሞኑ የአነግ ብልጽግና አገዛዝ ከወያኔ ጋር ስላደረኩት ስምምነት ማብራሪያ ልስጣችሁ ብሎ ሬዴዋን ሁሴን የተባለ ተጠሪ ስብስቧቸው ነበር።በዚህ ስብሰባ ላይ ምን እንደተነጋገሩ፣ምን ጠይቀው ምን መልስ እንዳገኙ እንኳን ለሕዝቡ አልገለጹም።የተሰማው ነገር ቢኖር የብልጽግና ተጎታች ፉርጎ ሆነው መዋላቸው ብቻ ነው ።

ለሰላማዊ ትግል የሙያ ድርጅቶችና ፣የእምነት ተቋማት በቂ ናቸው።ያም ትግል ቢሆን ገደብ አለው። መልስ ካልተገኘ ወደ ሌላ የትግል ደረጃ መሻገሩ አይቀሬ ነው። የብዙሃን ድርጅቶች ከሕዝብ የወጡ በመሆናቸው ለሕዝባዊው አመጽ አጋር ብቻም ሳይሆኑ ለአመጻዊ ትግል ቀፎ ይሆናሉ እንጂ ተጻራሪ አይሆኑም።የሃይማኖት ተቋማት ሰዎች በሃይማኖትና በሙያቸው የሚታረዱ ከሆነ አራጁን ለመከላከል ይገደዳሉ።መሣሪያ ያነሳሉ።በጾምና በጸሎት ወይም በመለመን የመጣባቸውን አደጋ ሊመልሱት አይችሉም። በተፈጥሮ ቀውስ የሚደርስባቸውን አደጋ በጸሎትና በንስሃ ፈጣሪያቸውን አቤት ማረን ሊሉ ይችላሉ።በሥርዓቱ የሚደርስባቸውን በደል ግን በጸሎትና በልመና ሊያሶግዱት

አይችሉም።ለነሱ የሚሆን ሥርዓት ለመፍጠር በሚያስችለው መንገድ መታገል ይኖርባቸዋል። ሕግ ያላስከበረውን መብትና ነጻነት ሃይል ያስከብረዋልና ወቅቱ በሚጠይቀው ትግል ውስጥ መሳተፋቸው ግዴታ ነው።ቤተ እምነት እየወደሙ፣ ምእመናን፣ቀሳውስትና ሽኮች እዬታረዱ እጅን አጣጥፎ መቀመጥ ከአጥፊዎቹ ጋር መተባበር ነው።ፍርሃት  በእራሱ ሃጢያት ነው።የወያኔ ኦነግ ብልጽግናን ሥርዓት አለመቃወም ሃጢያት ነው። ለነሱ የቆሙና በነሱ የሚመሩ የሃይማኖት መሪዎችን መከተል ሃጢያት ነው።የካዱት ምእመናኑን ብቻ  ሳይሆን ፈጣሪንም ጭምር ስለሆነ እንደ ሃይማኖት አባት ሊቆጠሩ አይገባም ።የጽዳት ዘመቻው ከነሱ ሊጀምር ይገባል።

ባለፈው ዝግጅታችን በቁጥር 44 ላይ እንደገለጽነው በባሪያ ሥርዓት መውደቂያ ዘመን በተደረገው ትግል መከራው የጠናበት የመስክ ባርያ(Field Slave) በመጀመሪያ እርምጃ የወሰደውና ቀጥቅጦ የገደለው ድስት በመላሱ  የተሻለ አያያዝና ክብር እንደተሰጠው ተሰምቶት፣ ለጌታው ጅራፍ ተሸካሚ ከዚያም አልፎ ጌታው ሲደከመው ተቀብሎ በሚገርፈው የማድ ቤት ባሪያ(kitchen Slave) በነበረው ላይ ነበር።ትግሉን የጀመረው በአቅራቢያው በሚገኘው ማድ ቤት ውስጥ የሚርመጠመጠውን ፣እሱን መሳይ የቅርብ ጠላቱን በማሶገድ ነበር።በአገራችንም

ጠላትማ ምን ጊዜም ጠላት ነው፣

አስቀድሞ መምታት አሾከሿኪውን ነው!የሚለው ምክር ያለነገሩ አይደለም።

በተመሳሳይም በአገራችን ለሰፈነው የጎሳ ሥርዓት መሣሪያና ምርኩዝ የሆኑትን የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሲቪክ ተቋማትና ለጥቅም ያደሩ ግለሰቦችን ማሶገድ ለትግሉ ውጤት ወሳኝ ነው።ትግሉ የጠራ ዓላማና ግብ ሊኖረው ይገባል።ጠላትና ወዳጁን የለዬና  ሰልፉም የጠራ መሆን አለበት።አድርባይ ተግበስብሶ የሚያቦካበት ሊሆን አይገባም።

ትግሉ ከመጨረሻው ወሳኝ ደረጃ ላይ ለመድረሱ የሚታዩትና የሚሰሙት ክስተቶች አመላካች ናቸው። በአዲስ አበባ በትምህርት ቤት ዙሪያ የሚደረገው ተቃውሞ፣የጋዜጠኞች አፈና፣ፋኖን የማሳደዱና በአጠቃላይ የአማራውን ትግል በሽኔነት መድቦ ለመጨረስ እቅድና መመሪያ መውጣቱ፣የወያኔና የኦነግ ብልጽግና ትብብር፣ለሥርዓቱ የምዕራባውያን በተለይም የአሜሪካኖች ድጋፍና ጣልቃ ገብነት፣እያዘቀዘቀ የመጣው የገንዘብ ግሽበት፣እያሻቀበ የሄደው የኑሮ ውድነት፣የሰላም እጦት፣ድህነት፣ሥራ አጥነት፣ስደት፣ ሌብነት፣ መዋቅራዊና መንግሥታዊ ሙስናና ዘረፋ፣ተስፋ መቁረጥ፣እራስ ወዳድነት፣ሽብርና ሥርዓተ አልበኛነት እነዚህ ሁሉ ለአንድ ሥርዓት ወይም አገር ውድቀት መመዘኛና አመላካቾች  ናቸው።የጎሰኞቹ ሥርዓት ሲወድቅ አገር ይዞ እንዳይወድቅ  ፣አገር ወዳዱ በአንድ ጣራ ስር መሰባሰብና የተቀናጀ ትግል ማካሄድ ይኖርበታል።በብሶትና በእልህ ብቻ የተበታተነ ትግል ማካሄድ ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል፤ ለጠላት ጥቃትም ያጋልጣል።

ያንን እውን ለማድረግ የአገር ወዳዶቹ ትግልና  ጥረት ቀጥሏል።ፋኖ እራሱን ለማዳን በመሰባሰብ ላይ ነው።የሚሰነዘርበትንም ጥቃት ለመቋቋም ወስኗል።በውጭም በውስጥም የተቃውሞ ድምጾች በመሰማት ላይ ናቸው።የአንድነት ጥሪዎችም ተላልፈዋል።የዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ማህበር፣ የአርማጭሆ የአማራ ማህበር፣የአማራ ወጣቶች ማህበር በአሜሪካና በአውሮፓ ሥርዓቱን የሚያጋልጥ መግለጫ በማውጣት  ለወሳኙ ትግል ጥሪ አድርገዋል።በተለይም የሴቶቹ ማህበር መግለጫ የጎሳ ሥርዓቱ ተገርስሶ በሕዝባዊ የሽግግር መንግሥት እንዲተካ በሚለው  የትግሉ አቅጣጫና መዳረሻ ምን መሆን እንዳለበት በግልጽ  ጠቁሟል።እኛም ይህንን እንደ ግብአት ተቀብሎ መሰለፍ ይገባል እንላለን። የዓላማ ጥራት ማለትም እንዲህ ነው።አብይ ይውረድ ማለት በቂ አይደለም፤ሥርዓቱ በአጠቃላይ

ተወግዶ በምን መተካት እንዳለበት መጠቀምና በዚያ ደረጃ መዘጋጀት ተገቢ ነው።ሰርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ ከሚለው እሩጫ ለመዳን ከአሁኑ የትግሉ ዓላማና ቅደም ተከተል መዘጋጀት አለበት።

ከቀጋ የተጠጋ ቁልቋል ዘላለም ያለቅሳል እንደሚባለው ሥርዓቱን አምነው የተጠጉና በውጭ አገር የሆነ ያልሆነውን ሥራ ሠርተው፣አገር ቤት ለሚገዙት ንብረትና ለሚያደርጉት አስረሽ ምችው መዝናናት እንጠቀምበታለን ብለው በአገር ቤት ባንክ ውስጥ ያስቀመጡትን ከ20 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገንዘባቸውን ካለ ይግባኝ በሚያምኑትና በሚደግፉት መንግሥት እንደተነጠቁ ሰምተናል።ሌላው በሁኔታው ሲስቅና ሲያላግጥ እኛም አተርፍ ባይ አጉዳይ ብለናቸዋል።ዶላሩን ወይም ኤሮውን በጥቁር መትቼ ብዙ ብር እሰበስባለሁ ብሎ ያጠራቀመ ከነዋናውም ማጣቱ ለሌላው ትምህርት ይሆናል። ወትሮም ቢሆን ሆዱን የወደደ የታሰበለትን አደጋ ለማዬት ይሳነዋል።አይጥ በወጥመዱ ላይ የተቀመጠውን የዳቦ ፍርፋሪ መዳረሻ ብታውቅ ኖሮ ለሞት አትዳረግም ነበር።በተመሳሳይም የሌባና የጎሰኞች ጥርቅም የሚፈልገውን ድጋፍ ለማግኘት ሲል የሚጠቀምበት ስልት ጊዜያዊ ጥቅም ሰጥቶ ከጊዜ በኋላ ተጠቅሞ መወርወር እንደሆነ የቡድኑ ቁንጮ አብይ አህመድ በጻፈው መጽሐፍ ላይ "የሚፈልጉትን አሳይተህ ወደምትፈልገው ንዳቸውና ከዚያም በሬ ሆይ ሳሩን አይተህ ገደሉን የሚለውን ተረት ተርተህ ሳቅባቸው" ሲል ገልጾታል።

ይህንን አባባሉን ምናልባትም በወያኔዎቹ ላይ አሁን ሥልጣን እንዲጋሩ አድርጎ ከሚደግፉቸው የትግራይ ቡድን ከነጠላቸው በኋላ ይጠቀምበታል ብለን እንጠረጥራለን።ለእኛ ግን ከሚፋቀሩ እርስ በርሳቸው ቢባሉ ምርጫችን ሲሆን ለዳግም እልቂት እንዳይዳርጉን ግን ሁለቱንም ማሶገዱ የተሻለ ምርጫችን ነው። የወያኔ ደጋፊ ትግራይ እናቶቹ እግር ላይ ወድቀው ለሰላም ሲማጸኑ እምቢ ብሎ የብዙ ሽህ የትግራይ ልጆችን ለሞት የዳረገ ከሃዲ ቡድን ዓላማው የሥልጣንና የጥቅም መሆኑን ከዚህ የድርድር ውጤት ካልተረዳና ለፈጸሙት ወንጀል ለፍርድ እንዲቀርቡ ሳይጠይቅ እያጨበጨበ ከቀረ ነገም ለጦርነት ተሰለፍ ቢሉት ፎክሮ ላለመውጣቱ ዋስትና የለንም። የሚመጣው የከፋ እንዳይሆን እዬተመኘን ግን ሊከሰቱ የሚችሉትን ማስቀመጡ ለመዘጋጀት ይረዳልና ከዚህ በታች ለማስቀመጥ ተገደናል።

ሊከሰቱ የሚችሉ ገጠመኞች(Possible Scenarios)

1 ወያኔና አነግ ብልጽግና ከሆነላቸው በሕገመንግሥቱ መሠረት በሚል ሽፋን አለያም ተባብረው አማራውን በመውጋት የያዛቸውን አጽመርስቶቹን ወልቃይትና ጠገሌን፣ራያና ቆቦን ነጥቀው ከዚያም አልፈው ተርፈው ሰሜን ወሎንና ደቡብ ወሎን ለመቀራመት ይተባበራሉ።

2 ወያኔና አነግ ብልጽግና በአውሮፓውያንና በአሜሪካኖች ድጋፍና ትእዛዝ የኤርትራን በመውረር ኢሳያስን ለማሶገድ ይንቀሳቀሳሉ

3 ወያኔና አነግ ብልጽግና በሥልጣንና ጥቅም ክፍፍሉ ፣በቤንሻንጉልና በግድቡ ዙሪያ የመሬት ቅርምትና የይገባኛል ጥያቄ ዳግም ሊጋጩ ይችላሉ

4 ወያኔ ከኤርትራ ተቃዋሚ ሃይሎች ጋር ተባብሮ ኢሳያስን አውርዶ ሲያልማት የኖረውን የትግራይ ትግርኛ አገር ምሥረታ እውን ለማድረግ ሊንቀሳቀስ ይችላል።ግን በኤርትራ ውስጥ ብዙ ደም መፋሰስና መከፋፈል ያስከትላል እንጂ በቀላሉ የሚሳካ አይሆንም።የማታ ማታ ግን በጎሳ መሳሳብ ወያኔ ከሰሜኑና ከምስራቁ ክፍል ጋር ሲቀራረብ፣ የሰሜን ምዕራቡ በሃይማኖቱም በምድራዊ አቀማመጡና በቋንቋው ምክንያት ከሱዳኖች ጋር ለመሆን መምረጡ አይቀርም።

4 በኢትዮጵያ ውስጥ ጠንካራ ሕዝባዊ መንግሥት ካልተመሠረተና መረጋጋት ከሌለ፣አማራው እራሱን ካላደራጀና ሃይሉን ካልገነባ ብሎም አንድነቱን ካላጠናከረ የሁሉም መቀለጃ ይሆናል፤ ኤርትራም በበኩሏ የአርማጭሆንና ያካባቢውን ለም መሬት ጠቅልሎ ለመያዝ የምትንቀሳቀስበት ዕድሉ ከፍተኛ ነው።

5 ወያኔና ኦነግ ብልጽግና ካልተወገዱ በተያዘው መንገድ ከቀጠሉ ኢትዮጵያን በማፈራረስ የየራሳቸውን አገር ሊመሠርቱ ይችላሉ።

6 የአፋር ሕዝብ ከአማራው ጋር ጠንካራ ህብረት ካልፈጠረ በአምስት ሃይሎች ማለትም በኦነግ ብልጽግና፣ በወያኔ፣በሻእብያ፣በሶማሊያና በጅቡቲ የቅርጫ ሲሳይ ይሆናል

7 የደቡብ ሕዝብ መሬቱን በኦነግ ብልጽግና ተስፋፊ ተነጥቆ ሞጋሳ ይሆናል፣የተረፈውም እርስ በርሱ እዬተጋጨ ይኖራል

ከዚህ ሁሉ መጭ አስከፊ አደጋ ለመውጣት ያለው መንገድ በኢትዮጵያዊነት መቆም ብቻ ነው።

አሁንም እንላለን!ሕዝብ ሆይ ወደ ቀልብህ ተመለስ!

1 ላለፉት 32 ዓመታት ተራ በተራ ሥልጣኑን እዬተቀባበሉ ሲጨቁኑህ፣ሲገሉህ፣ሲዘርፉህ የኖሩትን የህወሃት፣ኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና አመራሮች፣አባላትና ደጋፊዎች ለፈጸሙት የአገር ክህደት፣የሕዝብ እልቂት ለፍርድ እንዲቀርቡ አድርግ!የነሱ እርቅና ሰላም አንተን ለቀጣዬ መከራ እንደሚዳርግህ ተረዳ!

2 ለተመሳሳይ ሥርዓት በተረኛነት የሚጠባበቁትን፣በተለያዬ የጎሳ ማህበረሰብ ስም ታጥቀው ንፁሃንን የሚያርዱና የሚያሳርዱ፣ ጸረ ኢትዮጵያ ከሆኑ የውጭ ሃይሎች ጋር የተሰለፉትንም አብረህ አሶግድ!

3 የወደፊቱ ሕይወትህ ዋጋና ትርጉም እንዲኖረው፣ለተተኪውም ትውልድ የሚተርፍ ሃገር ለማስረከብ የሰፈነውን የጎሳ ሥርዓትና በሕገ-መንግሥት ስም የተጫነብህን የጥፋት ሰነድ አሽቀንጥረህ በመጣል ለአንተ ሰላም፣ለአገርህ አንድትና እድገት፣ለተተኪው ትውልድ ኩራት በሚያሰፍነው ሥርዓትና ሕግ ለመለወጥ ተባብረህ ተነሳ!

4 ከውጭ አገር ተጽእኖ ተላቀህ በራስህ ምሳሌ “ያገሩን በሬ ባገሩ ሰርዶ” ብለህ የገጠሙህን ችግሮች ለመፍታት በራስ የመተማመን መርሆን ተከተል! ሌላው እንዲያከብርህ እራስህን አክብር!

5 ችግርን የምታስወግደው ችግር ፈጣሪዎችን ስታስወግድ መሆኑን ተረድተህ የችግሮቹ ሁሉ ምንጭ የሆነውን የጎሰኞችን ሥርዓት አምክን!

ሕዝባዊ ሃይል ይመሥረት!

ወንጀለኞች ለፍርድ ይቅረቡ!!

የሽግግር መንግሥት ይቋቋም!!!

ኢትዮጵያ በአንድነትና በነጻነት ለዘላለም ትኑር!!